# PEOPLES ALLIANCE FOR FREEDOM AND DEMOCRACY (PAFD)

## OFFICE OF PRESIDIUM

Date: August 08, 2016

Tel: +49-15145279816
+44-7940624477

Ref.:

Fax:


## በሰላማዊ መንገድ የተቃውሞ ሰልፍ ባካሄዱ የኦሮሞ ዜጎች ላይ በተደጋጋሚ እየተፈጸመ ያለው አረመኔያዊ ግድያ የኢትዮጵያን የፖለቲካና  የደህንነት ቀውስ በእጅጉ ያባብሳል።

*ሰላማዊ ሰልፍ ባካሄዱ የኦሮሞ ዜጎች ላይ የሕወሃት ስርዓት የፈጸመውን የጅምላ ግድያ በተመለከተ*

*ከህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የተሰጠ መግለጫ*

የኦሮሞ ህዝብ በሕወሃት በሚመራው ኣምባገነን ስርዓት ላይ እያካሄደ ያለው ተቃውሞ ከህዳር 12 ቀን 2016ዓም ኣንስቶ በቀጣይነት እየተካሄደ ይገኛል። የኦሮሞ ህዝብ በመላው ኦሮሚያ ውስጥ በመንግስት ላይ ጠንካራ ተቃውሞ እያካሄደ ነው። የሕወሃት መንግስት ዜጎች ላካሄዱት የተቃውሞ ሰልፍ የሰጠው ምላሽ ጥይት በማርከፍከፍ የጭካኔ ግድያ መፈጸም ሲሆን በዚህም እስከ ኣሁን ከ670 በላይ የኦሮሞ ዜግች ተገድለዋል። በመቶዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ቆስለዋል። ከ50,000 በላይ የሚሆኑ ዜጎች በሚታወቁ እስር ቤቶችና ባልታወቁ ቦታዎች ታስረው ለቶርቸር ተጋልጠዋል። ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ዜጎች ደግሞ ታፍነው ተሰውረዋል። ከተገደሉት ዜጎች መካከል ኣብዛኞዎቹ የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ወጣቶች፣ ነፍሰጡር ሴቶችና ኣዛውንት ናቸው።

የሕወሃት መንግስት ሃይሎች ይህንን የግድያ ወንጀል በህዝቡ ላይ የፈጸሙት በጎዳና ላይ ብቻ ሳይሆን በምሽት የህዝቡን መኖሪያ ቤቶች ሰብረው በመግባት ጭምር ነው። ኣያሌ ዜጎች ከመኖሪያ ቤታቸው ተወስደው በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በወታደራዊ ካምፖች፣ ዜጎች በጅምላ በሚታጎሩባቸው ቦታዎችና ወደ ተለያዩ ያልታወቁ ስፍራዎች ተወስደው ታስረዋል።

ተመሳሳይ ሁኔታዎች በቤኒሻንጉል፣ በኦጋዴን-ሶማሊ፣ በጋምቤላ፣ በኣማራ፣ በሲዳማ፣ በኮንሶ፣ በደቡብ-ኦሞና በተቀሩትም የሃገሪቷ ኣካባቢዎች በግልጽ እየታዩ ናቸው። የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በኦሮሚያ ውስጥ እየተካሄደ ባለው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ግንዛቤ እንዲጨበጥ ለማስቻልና የኢትዮጵያ መንግስት በህዝቡ ላይ እየፈጸመ ያለውን እርምጃ በተመለከተ በስፋት ዘግበዋል። የኣውሮፓ ህብረትና የኣመሪካ የኮንግረስ ምክር ቤት የተቃውሞ ሰልፍ ባካሄዱ የኦሮሞ ዜጎች ላይ በስፋት እየተፈጸመ ባለው ግድያ፣ እስራትና ሰቆቃ ያላቸውን "ስጋት" በመግለጽ የኢትዮጵያ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግድያና እንግልት እንዲሁም በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በማህበራዊ ዘርፎች እያደረሰ ያለውን ስልታዊ መድልዖና ማግለል እንዲያቆም ጠይቀዋል።

ነሃሴ 6 ቀን 2016ዓም የደረሰው የጅምላ ግድያም ከመላው ኦሮሚያ ውስጥ በኣንድነት በመውጣት በመንግስት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለጽና መሰረታዊውን የሰብዓዊና የፖለቲካ በመብቶቻቸውን ለመጠየቅ ሰልፍ በወጡ የኦሮሞ ዜጎች ላይ የተፈጸመ ነው።

የዚህ ዙር ተቃውሞ ዋና ከተማይቷ ፊንፊኔን ጨምሮ ከ200 በላይ በሚሆኑ የኦሮሚያ ከተሞች ውስጥ ተካሂዷል። እንደካሁን ቀደሞቹ ሁሉ ይህ ሰልፍም የመንግስት ሃይሎች የወሰዱትን የጭካኔ እርምጃ ኣስተናግዶ የበርካታ ሰዎች ህይወት ተቀጥፏል፣ በመቶዎች ቆስለዋል፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ መታሰርና ታፍነው መሰወር ኣጋጥሞኣቸዋል። በዚህ ዙር የተቃውሞ ሰልፍ ከ70 በላይ የኦሮሞ ዜጎች እጅግ ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ሲገደሉና ሲደበደቡ፣ ከ3,000 በላይ ደግሞ ወደ ተለያዩ ወህኒ ቤቶች ተወስደዋል፣ ታፍነው የተሰወሩት ቁጥራቸው ኣይታወቅም። ከኦሮሚያ ዞኖች ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ኣካባቢዎች ምስራቅ ሀረርጌ ኣወዳይና ሀረማያ፣ ምዕራብ ኣርሲ -ኣሳሳ፣ ባሌ -ዶዶላና ሮቤ፣ ምዕራብ ሸዋ -ኣምቦና ወሊሶ እንዲሁም ምስራቅ ወለጋ -ነቀምቴና ሌሎችም ይገኙበታል።


**Email: pafd22102015@gmail.com* 806B  Kennedy St. NW, Washington, DC 20011 * www.peoplesAFD.org ***

እኛ፣ 67% የሚሆኑ የኢትዮጵያ ህዝቦችን የሚወክለው **የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ** ኣባል ድርጅቶች መንግስት በሰላማዊ መንገድ ሰልፍ በወጡ የኦሮሞ ዜጎች ላይ የፈጸመውን የጭካኔ እርምጃ በጥብቅ እናወግዛለን። የሕወሃት መንግስት የኢትዮጵያ ኢምፓዬር ብዙሃን ማህበረሰብን መብት በግልጽ ጥሏል ብለን እናምናለን። ይህም የሕወሃት ቡድን ላለፉት 25 ዓመታት የራሱን ህገ-መንግስትና የኣለምኣቀፍና የቀጣናውን ህጎች በመጣስ በኦሮሞ ህዝብና በሌሎችም ተጨቋኝ ህዝቦች ላይ ከባድ ወንጀልና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትን እየፈጸመ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የህዝቦችን ድምጽ ለማፈን ሆን ተብሎ እየተወሰደ ባለው እርምጃና የህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን ወደ ጎን በመተው እየደረሰ ባለው ኣደጋ ከፍተኛ ስጋት እንዳደረበት ይገልጻል። የኢትዮጵያ መንግስት ህዝቦች እያቀረቡት ላለው መሰረታዊ ጥያቄ -የፖለቲካዊና የኢኮኖሚ መብቶችን ችግር ላለመፍታትና የህዝቦችን ጥያቄ የመልካም ኣስተዳደር እጦት ነው በሚል ኣቅጣጫውን ለውጦ ማቅረቡ ሃገሪቷን የከፋ ኣደጋ እንዲያጋጥማትና ለቀጣናው ኣለመረጋጋት የጎላ ድርሻ ያበረክታል ብለን እናምናለን። ይህ የህዝቦችን ጥያቄ በማጣመም የማቅረብ ሂደት ችግሩን ከመፍታት ይልቅ የህዝቡን ተቃውሞና ኣመጽ ይበልጥ በማስፋፋትና በማጠናከር የፖለቲካና የደህንነት ቀውስ መላውን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የኣፍሪካ ቀንድ ቀጣናን በማናጋት ለሽብርተኝነት መንገድ ይከፍታል።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ(PAFD) የኢትዮጵያ ኣጋሮች ቀድሞውንም የወደቀችዋን ሃገር በመልካም ኣስተዳደር ስም ለመጠጋገን እያደረጉት ያለው ጥረትና ስርዓቱ ዘግናኝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየፈጸመ በእርዳታ መደጎም በመቀጠላቸው ስጋታችን ከፍተኛ መሆኑን እንገልጻለን።

ይህ የሕወሃት መንግስት እያደረሰ ባለው ዘግናኝ ግድያ ጆሮኣቸውን የመዝጋት ተግባር በእጅጉ ያሳዘነን ሲሆን፡ ይህም የሕወሃት/ኢህኣዴግ መንግስት ነፍሰጡር እናቶችና ኣዛውንትን ጨምሮ በኦሮሞ፣ በኦጋዴን፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል፣ በኮንሶና በሌሎችም ኣካባቢዎች በሚገኙ ዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለውን የጅምላ ግድያ እንዲቀጥል መፍቀድ ነው። ይህን የሕወሃት ስርዓት እያደረሰ ያለውን ኣሰቃቂ እልቂት በዝምታ መመልከት ከሰብዓዊ ፍጡር የሚጠበቅ ኣይደለም። ስለሆነም የኣሜሪካ በመንስግት፣ የኣውሮፓ ህብረት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ሌሎችም የኢትዮጵያ ሽሪክ የሆኑ ሃገራት የከፋ ውድቀት ላይ ካለውና የሚያስተዳድራቸው ዜጎች ላይ ጭቆና፣ ከባድ ወንጀልና ሽብር እየፈጸመ ካለው የኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ኣቋማቸውን በድጋሚ እንዲመረምሩ እንጠይቃለን።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የኢትዮጵያ መንግስትና ኣጋሮቹ ተቃዋሚዎችን ወደ ጎን መተውና ከባድ ኣደጋ የደቀነውን የማግለንና የመነጠል ፖሊሲ ለማስቆም እንዲሰሩ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

ሰላምና መረጋጋት በተለይ በኢትዮጵያ ምድር ባጠቃላይ ደግሞ በኣፍሪካ ቀንድ ቀጣና እንዲረጋገጥ የህግ የበላይነትና የዲሞክራሲ ስርዓት ጽንሰ-ሃሳቦች ጊዜው ሳያልፍ ኣሁኑኑ በቋሚነት መከበር ኣለባቸው። ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያ መንግስት ኣጋሮች የሕወሃት ስርዓት በኦሮሚያ፣ በኦጋዴን፣ በሲዳማ፣ በቤኒሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በኮንሶ፣ በከፋ-ሸካ፣ በኦሞ ሸለቆ፣ በኣማራና በተቀሩትም የሃገሪቷ ኣካባቢዎች የዘር-ማጥፋት ወንጀልን ጨምሮ የተለያዩ ወንጀሎችን ለመፈጸም የሚጠቀምበትን የፋይናንስ፣ የፖለቲካና የደህንነት እርዳታ ለሕወሃት ስርዓት ከመለገስ እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሽሪኮች በሕወሃት የተፈጸመውን ግድያና ቶርቸር የሚያጣራና ወንጀለኞችን ለፍርድ የሚያቀርብ ነጻና ገለልተኛ ኣካል እንዲያቋቁሙ ኣጥብቀን እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ጦርና ደህንነት ሃይል ኣባላት የሆናችሁ ዜጎች ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ባጠቃላይ ወገናችሁን መግደሉን በማቆም ወደ ህዝባችሁ ትግል በመቀላቀል የሁሉንም ህዝቦች መብት የሚያስጠብቀውን እውነተኛ ለውጥ ለማስገኘት እንድትሰሩ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። በኦጋዴን ውስጥ የምትገኙና ወያኔን በማገልገል ላይ ያላችሁ የልዩ ፖሊስ ኣባላት ስልጣን ላይ ያለውን ስርዓት እድሜ ለማራዘም በሚል የኦሮሞና የሶማሌ ህዝቦችን ከማጋጨት እንድትቆጠቡ እንጠይቃለን።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ውስጥ የምትገኙ ህዝቦች ሁሉ የኢትዮጵያን ህዝቦች ፍትሃዊ ትግል ወደ ፊት ለማራመድና ከግቡ ለማድረስ ወደ ህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ እንድትቀላቀሉና ከጎኑ እንድትቆሙ ጥሪያችንን እናድሳለን። በኣንድ ድምጽና በጋራ ክንድ በመንቀሳቀስ የሽግግር ስርዓትና ህዝቦች የተመኙትን ለውጥ እውን ለማድረግ የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ እያቀረበ ያለውን ጥሪ በመቀበል ዓላማውን ለማሳካት እንድንሰራ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

**የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የፕሬዚዲዬም ጽህፈት ቤት**

**ነሃሴ 8 ቀን 2016ዓም**

**Email: pafd22102015@gmail.com* 806B Kennedy St. NW, Washington, DC 20011 * www.peoplesAFD.org ***